homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
12 ሳተን ስትሪት
ኖርዝ ሜልበርን

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 ሰፈሮች ወይም ሳበርቦች ለሚኖሩ የአሁኑ እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ የሆኑ ቤቶች ወደ ማቅረቡ እያመራን ነው።

የዛሬው ማስታወቂያ በአካባቢያችሁ ያሉትን ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል ስለሆነም በእነዚህ ሕንፃዎች ውስጥ ከሚኖሩ ነዋሪዎች ጋር በመደበኛነት እንገናኛለን። **በቤትዎ ወይም በህንጻዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፦

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፐራሃን
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣ የተሻሉ እና ብዙ ቤቶችን በምናቀርብበት ጊዜ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲዛወሩ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## በአቅራቢያዎ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

እነዚህን ነዋሪዎች በአቅራቢያ ባሉ የመዘወሪያ አማራጮች እንዲኖሩዋቸው ለመደገፍ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች በመስራት ሂደት ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፕራሃን
- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ፣ ደህንነትን፣ ብርሃን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች ይኖራቸዋል።

## በሰፈራችሁ

በ33 አልፍሬድ ስትሪት ላይ የቀሩ ጥቂት አባወራዎች ዝውውራቸውን ለማጠናቀቅ ን እየደገፍን ነው። እንዲሁም ለአዳዲስ ቤቶች እና የማህበረሰብ መገልገያዎች ዲዛይኖች ላይ የነዋሪዎችን ግብአት ግምት ወስጥ እያስገባን ነው። ራዕዩ በጥሩ ሁኔታ በተነደፈ እና በደንብ በተገናኘ ሰፈር ውስጥ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች መገንባት ነው።

## ስለ መልሶ ማልማት ፕሮግራም

የሜልበርን የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዘመናዊ የምቾት፣ የተደራሽነት እና የኃይል (ኢነርጂ) ቆጣቢነት ደረጃዎችን በሚያሟሉ አዳዲስ ቤቶች ይተካሉ። እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና በማልማት ነዋሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ምቹ እና አሁን እና ወደፊት ለፍላጎታቸው ተስማሚ በሆኑ ቤቶች ውስጥ መኖር እንደሚችሉ እያረጋገጥን ነው።

ከጃንዋሪ 2028 በፊት የሚጀመር ተጨማሪ ከሰማይ ጠቀስ ፎቅ የማዛወር ሂደት አይኖርም።

## ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስዎ ከኛ ጋር መገናኘትዎ አያቋርጡ

ቤትዎ በዚህ የሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት ደረጃ አካል አይደለም፣ ነገር ግን በአካባቢዎ ውስጥ ለውጦች ሲከሰቱ ሊያስተውሉ ይችላሉ። በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ ከእርስዎ ጋር መገናኘታችን አናቋርጥም።

እንዲሁም በአቅራቢያዎ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማየት እና የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመቀበል ለመመዝገብ homes.vic.gov.au ድህረ ገጻችንን መጎብኘት ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026